# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)

*Ethiopian People´s Revolutionary Party (EPRP)*

**ጥቅምት 12 ቀን 2010 ዓ.ም.**

## ተቃውሞው ተቀናጅቶ የወያኔን ውድቀት ያፋጥን

የፍርሃትንና  የልዩነትን ግንብ አፍርሶ በተለያየ የአገራችን ክፍል ያለው ሕዝብ በትግሉ መድረክ አለና ካለ ጀምሮ ወያኔ ባለው የአፈና አቅም ሁሉ ሺዎችን ገድሎ፤ ብዙዎችን አግቶና ለስየል ዳርጎ ትግሉን ሊያፍን ቢሞክርም  የሕዝብ አመጽ ቀጥሎና ግሎ ወያኔን እያርበደበደ መሆኑ እየታየ ነው ። የወያኔ የውድቀት ደወል ተደውሎ ደወሉም በሀገራችን በሞላ እየተደመጠ ነው ።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በየአቅጣጫው በተለያዩ ከተሞች ሕዝብ ጸረ ወያኔ ሰልፍና ትግልን እያፋፋመ ባለበት ወያኔ በሚችለው የማደናገሪያ ሙከራ ሁሉ ተሰማርቶ ክፍፍልን በማፋፋም፤ ስልጣን ልንለቅ ነው ብሎ ቧልትን በማሰራጨት፤ ግድያውን ሳይታክት በማካሄድ፤ ቅጥረኞቹን በሀገር ቤትም በውጭም በማሰማራት፤ ወዘተ በስልጣን ሊቀጥል እየጣረ ነው ። የስውርና የይፋ ቅጥረኞቹም በጥረቱ ተካፋይ ሆነው የሀገር ወዳዶችን ትግል ለማደናቀፍ በየፊናቸው እየዘመቱ ናቸው ። ይህ ሁሉ ግን ስኬትን አላገኘም ። ሀገራችን በተቃውሞ እየተናጠች ሲሆን የወያኔም የርስ በርስ ሽኩቻ ተባብሷል። የሚጠበቅና ልናባብሰው የሚገባ ነው ። አዲስ አበባም አመጽን አርግዛ ትገኛለችና ውልደቱ የተሳካ እንዲሆን ማዘጋጀቱ የሁሉ ሀገር ወዳድ ግዳጅ መሆን እንዳለበትም ግልጽ ነው ። አስፈላጊ የሆነውን ዴምክራሲያዊ ሽግግር እንደገና ሊያደናቅፉን ወያኔዎች፤ ጽንፈኞች፤ የወያኔ የባዕድ ወዳጆች፤ ሻዕቢያ፣ የቅርብና የሩቅ ጠላቶችም እየሞከሩ ነው ። የህገራችንን መሬት በወያኔ ለጋሽነት የተረከበው ሱዳንም የለመደባቸውን ከሀዲዎች ከወያኔ ለማግባባትና እንደ 1981 ኡ የሕዝብን ትግል ለማፈን በመራወጥ ላይ ነው ። ይህ ሁሉ ሊሳካላቸው ባይችልም ጭራሽ ውድቅ እንዲሆን ሁላችንም ሀገር ወዳዶች መረባረብ እንዳለብን ግልጽ ነው ።  እየተካሄደ ያለው ትግል የሚቀረው ቅንጅት ነው። በሁሉም ቦታ በጋራና በተቀናጀ መልክ በሀገር አቀፍ ደረጃ የሙት ከተማን አድማ ማፋፋም ። በሀገር አቀፍ ደረጃ ጠቅላላ የስራ ማቆም አድማ ማካሄድ። በአገሪቱ በሞላ የተቃውሞ ሰልፎችን ቀጣይ በሆነ መንገድ ማካሄድና ለዚህ መዘጋጀት ወሳኝ ነው ። ወያኔ የሕዝብ ጎራ አባል መስሎ አስመሳይና አደናጋሪ ጥሪዎችን እንዳያደርግና እንዳያከሽፍም ተገቢው ጥንቃቄ መደረግ አለበት ። ሕዝብን እርስ በርስ ሊያጋጭ ደፋ ቀና ይላልናም ይህ እንዳይሆን ሁሉም ዜጋ ነቅቶ እምቢኝን ማሰማትና አንድነትን ማጠናከር ይጠበቅበታል ።

**EPRP**
**P.O.BOX 73337**
**Washington DC, 20056**
**USA**

**Email [ESPIC@aol.com](mailto:ESPIC@aol.com)**
**Website [www.eprp.com](http://www.eprp.com)**

**EPRP**
**BP 30022**
**92276 Bois Colombes cedex**
**France**

**Tel. 202 291 4217    Fax: 202 291 7645**

ኢሕአፓ፣ በወያኔ ላይ የሚደረገው ተቃውሞ ሀገራዊ ቅንጅት እንዲይዝና የተባበረ እንዲሆን ጥሪውን ያስተላልፋል፤ ለዚህም ይዋደቃል። በዚህ በመጨረሻውም ወቅት የወያኔ ቅጥረኛ ሆነው የሀገር ወዳዶችን ትግል ለማደናቀፍ የሚፍጨረጨሩትንም ጊዜ አልፎባቸኋል እያለ በጊዜ እንዲታረሙ ማስጠንቀቂያውን ማስተላለፍ ይወዳል ። የተናጠል ትግል በጋራ ትግል ይተካ የሚለው ጥሪ እየተሰማ በመሆኑ የጋራና ጠቅላላ ሕዝቡን የሚያንቀሳቅሱ አድማዎች እውን እንዲሆኑ በህብረት እንጣርም ይላል ። የሀገር አድን ትግሉ እንቅፋት ሊሆኑ የሚጥሩትን የወያኔና የባዕድ ቅጥረኞችንም ነቅተን በመታገል ባዶ እናስቀራቸው። የወያኔን ሀገር አጥፊ ዕቅድም ውድቅ እናድርገውና እንደነታችንን እናጠናክር።

የኢትዮጵያ ሕዝብ በወያኔ ላይ ድልን ይቀዳጃል !

እናቸንፋለን !!